**ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን)**

ጥር 21፣2004 ዓም

# ከመከላከያ በተተኮሰ ጥይት ሶስት ሰዎች ሲገደሉ ሁለት ቆሰሉ

በጋምቤላ ክልል ፉኚዶ ከተማ የመከላከያ ማዘዣ ጣቢያ ውስጥ በድንገት በተከፈተ ተኩስ ሶስት ሰዎች ሲሞቱ ሁለት መቁሰላቸው ተሰማ። ለደህንነታቸው ሲሉ ስማቸውን ከመግለጽ የተቆጠቡት የአካባቢው ምንጮቻችን እንዳስታወቁት በድንገት አካባቢውን አሸብሮ የነበረው ተኩስ መነሻው ማንነታቸው የማይታወቅ ሰዎች ወታደራዊ የማዘዣ ጣቢያ ውስጥ ዘልቀው ገብተዋል በሚል ስጋት ነው።

ጥር 19 ቀን 2004 ዓ ም ከሌሊቱ 8፡00 ሰዓት ገደማ ማንነታቸው ያልታወቀ ሰዎች በወታደራዊ ካምፑ ውስጥ መታየታቸውን ተከትሎ በያቅጣጫው መተኮስ የጀመሩት በጋምቤላ እየተስፋፋ ያለውን የመሬት ነጠቃ የሚቃወሙትን ለመቆጣጠር በክልሉ የተሰማሩት የመከላከያ ሠራዊት አባላት ናቸው።

ሰፋፊ መሬት እየወሰዱ ያሉትን የውጭ ባለሃብቶችን የሚቃወሙ በመበርከታቸው በየጊዜው የመከላከያ ሰራዊት ቁጥር መጨመሩን የሚገልጹት የዓይን እማኞች፣ በክልሉ ውጥረት መባባሱን ይናገራሉ።

**“መሬታችንን ተነጥቀን ከምንኖር መሞት ይሻለናል. . .”** በማለት ጫካ የገቡ እንዳሉ ያስታወሱት ምንጮች፣ **“ጫካ የገቡት ሽፍቶች መሳሪያ ስለመታጠቃቸው የሚታወቅ ነገር ባይኖርም ቁጥራቸው ቀላል አይደለም፤ ራሳቸውን የማደራጀትም አቅም ያላቸው ይመስላል”** ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

በዕለቱ በፍርሃቻ ስለተከፈተው ተኩስና ስላስከተለው ጉዳት እንዲያስረዱ የተጠየቁት የመረጃው ባለቤቶች **“በመከላከያ ግቢ ውስጥ በድንገት የተጀመረው ተኩስ መነሻው በትክክል ባይታወቅም ማንነታቸው ያልታወቀ ሰዎች ወታደራዊ ማዘዣውን ዘልቀው በመግባታቸው ሲሆን፣ አደጋ የደረሰባቸው ሰዎች በሌሊት እንቅልፍ ላይ የነበሩ ናቸው”** ብለዋል።

የመከላከያ ቅጥር ዘልቀው ከገቡት መካከል የተያዘ፣ የቆሰለ ወይም የተገደለ ባለመኖሩ ምንም ዓይነት መረጃ ማግኘት እንዳልቻሉ ያመለከቱት የመረጃው ምንጮች፣ ህይወታቸው ካለፉት ሰዎች መካከል እንቅልፍ ላይ እያለች የመከላከያ ሠራዊት ጥይት የገደላት እናት አስከሬን ለምርመራ በሚል በፖሊስ ሲወሰድ፣ እናቷን ያጣችውና የመቁሰል አደጋ የደረሰባት ታዳጊ የህክምና ርዳታ እንደተደረገላት አመልክተዋል። በተመሳሳይ አንድ ክፉኛ ቆስሎ የነበረ ሰው የህክምና ርዳታ ሲደረግለት እንደነበር ቢገለጽም ህይወቱ ሊተርፍ እንዳልቻለ ለማወቅ ተችሏል። በሊስትሮ ስራ የተሰማራው ሌላው ሰለባ በተኛበት በጥይት ጉዳት ደርሶበት የህክምና ርዳታ ከማግኘቱ በስተቀር ጤንነቱ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ዝርዝር መረጃ ማግኘት እንዳልቻሉ ምንጮቻችን አስረድተዋል።

ሁኔታው በፈጠረው ስጋት አገዛዙ በስፍራው ያሰማራቸው አንጋቾች ለአሰሳ ወደ ጫካ አምርተዋል። የአሰሳው ወጤት ባይታወቅም በጋምቤላ ለውጭ ባለሃብቶች እየተሰጠ ያለው መሬትና ፕሬዚዳንቱ አቶ ኦሞት ከኃላፊነታቸው እንዲነሱ ከተወሰነ በኋላ ውሳኔው መገልበጡ በክልሉ ያለውን ውጥረት አባብሶታል። **በድንገት ተከፈተ**

**በተባለው በዚሁ የጥይት እሩምታ ጉዳት ያደረሱት የሰራዊት አባላት ላይ ርምጃ ስለመወሰዱ፣ ለጥያቄም ቢሆን የወረዳው ፖሊስ ጠርቶ ያነጋገራቸው አካላት ስለመኖራቸው የሚያውቁት ነገር እንደሌለ የፖሊስ ምንጮቻችን ተናግረዋል። አያይዘውም በክልል ደረጃም ቢሆን ህይወት ያጠፉትንና የአካል ጉዳት ያደረሱትን የመከላከያ አባላት በህግ ተጠያቂ ለማድረግ የተጀመረ እንቅስቃሴ እንደሌለም አመልክተዋል።** በድርጊቱ የተበሳጩ የከተማዋ ነዋሪዎችም በዚሁ ሳቢያ ቅሬታቸውን እየገለጹ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል።

ከጥቂት ሳምንታት በፊት በተካሄደ ግምገማ ከፓርቲው መሪነት ሥልጣን የተወገዱት አቶ ኦሞት ኦባንግ **“እኔ ከታሰርኩ ወታደርና መሣሪያ የሰጠኝ አቶ መለስም ይታሰራል”** ማለታቸው ይታወሳል። በዚህ ንግግራቸው ፕሬዚዳንቱ ከስምንት ዓመታት በፊት ስለተጨፈጨፉት ከ400 በላይ የአኙዋክ ብሄረሰብ አባላት አቶ መለስን በቀጥታ ተጠያቂ አድርገው ነበር። ይኸው የፕሬዚዳንቱ ንግግር የፈጠረው ስሜት በህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ውስጥ ከፍተኛ ሽብር ከመፍጠር አልፎ ማስተባበያም ሆነ ምላሽ ለመስጠት ያልተቻለበትና ጭንቀትን የፈጠረ ታላቅ ቀውስ እንደሆነ በስፋት እየተነገረ ይገኛል፡፡

## ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን)

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን) የሚዲያና ሕዝብ ግንኙነትን (media@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት ለመረዳት ይችላሉ፡፡*

